የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፷/፲፱፻፸ ዓ. ም.

## የእርሻ ልማት ድርጅቶች ደንብ

**፩። አውጪው ባለሥልጣን ።**

የእርሻና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስትር በመንግሥት እርሻዎች ልማት ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፸ ዓ.ም. በአንቀጽ ፲፫ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

**፪። አጭር ርዕስ ።**

ይህ ደንብ «የእርሻ ልማት ድርጅቶች ደንብ ቁጥር ፷/፲፱፻፸ ዓ.ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

**፫። ትርጓሜ ።**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩/ «ባለሥልጣን» ማለት የመንግሥት እርሻዎች ልማት ባለሥልጣን ነው ፤

፪/ «አዋጅ» ማለት የመንግሥት እርሻዎች ልማት ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፸ ዓ. ም. ነው ፤

፫/ «ድርጅት» ማለት በመንግሥት እርሻዎች ልማት ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር ፻፵፪/፲፱፻፸ ዓ. ም. መሠረት የሚቋቋመው ማንኛውም የእርሻ ልማት ድርጅት ሲሆን ፣ የሚከተሉትንም ይጨምራል ፤

ሀ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፳፯/፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የተቋቋመው ላይኛው አዋሽ የእርሻ ልማት ድርጅት፤

ለ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር ፳፰/፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የተቋቋመው መካከለኛው አዋሽ የእርሻ ልማት ድርጅት ፤

LEGAL NOTICE No. 60 OF 1978

## AGRICULTURAL DEVELOPMENT CORPORATIONS REGULATIONS

**"ETHIOPIA TIKDEM"**

1. *Issuing Authority*

These Regulations are issued by the Minister of Agriculture and Settlement pursuant to authority vested in him by Article 13 of the State Farms Development Authority Proclamation No. 142/1978.

2. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Agricultural Development Corporations Regulations No. 60/1978."

3. *Definitions*

In these Regulations, unless the context otherwise requires:

(1) "Authority" shall mean the State Farms Development Authority;

(2) "Proclamation" shall mean the State Farms Development Authority Proclamation No. 142/1978.

(3) "corporation" shall mean any agricultural development corporation established by the Minister of Agriculture and Settlement pursuant to the State Farms Development Authority Proclamation No. 142/1978 and includes:

(a) the Upper Awash Valley Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 27/1976;

(b) the Middle Awash Valley Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 28/1978;

ሐ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፳፱/ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. የተቋቋመው ስምጥ ሸለቆ የእርሻ ልማት ድርጅት ፤

መ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፴፪/፲፱፻፷፰ ዓ. ም. የተቋቋመው ሐረርጌ የእርሻ ልማት ድርጅት፤

ሠ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፴፫/፲፱፻፷፰ ዓ. ም. የተቋቋመው ተንዳሆ የእርሻ ልማት ድርጅት፤

ረ) በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቍጥር ፴፯/ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የተቋቋመው ገዋኔ የእርሻ ልማት ድርጅት ።

፬ ፤ የደንቡ ተፈጻሚነት ፤

ይህ ደንብ በድርጅቶች ሁሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፭ ፤ የሕግ ሰውነት ፤

እያንዳንዱ ድርጅት የራሱ የሆነ የሕግ ሰውነት አለው። ስለዚህም የመክሰስና የመከሰስ ችሎታ ይኖረዋል ።

፮ ፤ ስለ ድርጅት ዋና ገንዘብ (ካፒታል) እና ኃላፊነት ፤

፩/ የማንኛውም ድርጅት ቀና ገንዘብ (ካፒታል) ፤ በተለይ ያለማው ወይም እንዲያለማው የተመደበለት ወይም የሚመደብለት መሬት በሕግ የተጠበቀ ነው ።

፪/ የመቀላቀል ሥነ ሥርዓት በሚደረግበት ጊዜ ጠቅላዩ ድርጅት ወይም በመቀላቀል የተገኘው አዲስ ድርጅት የቀሩት ድርጅቶች ያለሙት ወይም እንዲያለሙት ተመድቦላቸው የነበረውን መሬት ይወርሳል ፤

፫/ ማናቸውም ድርጅት ከንብረቱ በላይ ዕዳ እንዲከፍል ሊጠየቅ አይችልም ።

፯ ፤ የድርጅቶች ተግባርና ሥልጣን ፤

እያንዳንዱ ድርጅት በአዋጁ በተሰጠው ተግባርና ሥልጣን መሠረት በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ዓላማዎቹን ለመፈጸም የሚያስፈልገው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል ። በተጨማሪም የባለሥልጣኑ አጠቃላይ የመቆጣጠር ተግባርና ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ የሚከተሉትን ለማድረግ ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል ።

፩/ ገንዘብ ፤ ንብረት እና ሌላ ዓይነት ካፒታል ድርጅቱ ለተቋቋመበት ዓላማ በሥራ ላይ ለማዋል ፤

፪/ ገንዘብ ለመበደር ፤ የንግድ ሰነዶችን ለማውጣትና ለመቀበል እና የሚንቀሳቀሱ እና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በመያዣነት ለመስጠት ፤

፫/ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ ለመሆን እና በንብረቱ እንዳስፈላጊነቱ ለመጠቀም ፤

፬/ በራሱ ስም የባንክ ሂሣቦች ለመክፈትና ሂሳቡን ለማካሄድ ፤

፭/ የመንግሥት መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከውጪ አገርም ሆነ ከአገር ውስጥ ከማንኛውም ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ካለው ድርጅት ጋር ለመዋዋል።

፰ ፤ የየድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ሥልጣን ፤

፩/ የእያንዳንዱ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ለተሾመበት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሹም ስለሆነ ፤ በባለሥልጣኑ ጠቅላላ ቍጥጥር የድርጅቱን ሥራ እና አስተዳደር ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ።

፪/ ከዚህ በላይ ባጠቃላይ የተመለከተው ሳይነካ ፤ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ፤

(c) the Rift Valley Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 29/1976;

(d) the Hararghe Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 32/1976;

(e) the Tendaho Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 33/1976, and

(f) the Gewane Agricultural Development Corporation established under Legal Notice No. 37/1976.

4. *Scope of Application*

These Regulations shall apply to all corporations.

5. *Juridical Personality*

Each corporation shall have juridical personality and, as such, can sue and be sued.

6. *Capital and Liability of the Corporations*

(1) Every corporation's capital, land in particular, whether developed or not, shall be protected by law.

(2) In case of amalgamation, the corporation taking over or the new corporation resulting from the amalgamation, as the case may be, shall take over all the assets and land, whether developed or not, of the corporation or corporations, as the case may be, ceasing to exist.

(3) No corporation may be held liable beyond its assets.

7. *Powers and Duties of Corporations*

Each corporation shall, under the general direction of the Authority, in accordance with the Proclamation, have such powers as are necessary to accomplish its purposes including, subject to the general supervision of the Authority, the power to:

(1) invest and expand money, goods and other forms of capital in order to achieve its purposes;

(2) borrow money, issue and accept commercial or other instruments and pledge and mortgage movable or immovable property;

(3) own, possess and dispose of movable and immovable property as is deemed necessary;

(4) open and operate bank accounts in its name;

(5) without prejudice to government directives, enter into contracts with any natural or juridical person, foreign or domestic.

8. *Powers and Duties of the General Manager of Each Corporation*

(1) The General Manager of each corporation shall be the chief executive officer of the corporation to which he is appointed and shall direct and supervise its operations and management subject to the general direction of the Authority.

(2) Without limiting the generality of the foregoing, the General Manager shall, in accordance with the directives to be issued by the Authority:

ሀ) ገንዘብ ይበደራል ፤

ለ) ሕንፃ ቤት ፤ ልዩ ልዩ ዕቃዎች እንዲሁም ተሽከርካሪ መኪናዎችንና የመሳሰሉትን ቋሚ ሀብቶች ይገዛል ፤ ይሸጣል ፤ በመያዣነትም/ ይሰጣል ።

ሐ) በባንክ ሂሳብ የተቀመጠውን ገንዘብ ያወጣል፤

መ) ከፍርድ ቤት ውጪ ክርክሮችን በስምምነት ይጨርሳል ።

፫/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ፤

ሀ) የባንክ ሂሣቦችን በመክፈት ገንዘብ ያስቀምጣል ፤

ለ) ድርጅቱ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ጉዳይ ሁሉ ድርጅቱን ይወክላል ፤ ወይም ድርጅቱን የሚወክል ሰው ይሾማል ፤

ሐ) የድርጅቱን የውስጥ ደንብ አዘጋጅቶ ባለሥልጣኑ እንዲያጸድቅለት ያቀርባል ፤

መ) የድርጅቱን ማንኛውንም ሠራተኛ እና ሥራ መሪ ይቀጥራል ፤ ከሥራም ያሰናብታል ፤ ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው መሠረት ደመወዛቸውንና ማናቸውንም ክፍያዎች ይወስናል ።

፬/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው ጠቅላላ መመሪያዎች መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ ፤

ሀ) የሥራ አመራርን ፤ ሰብል ማምረትን ፤ ዕቃዎች ሠርቶ ማውጣትንና አገልግሎቶች መስጠትን ፤ ሰብሎችንና ዕቃዎችን መሸጥንና ለሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችንና አገልግሎቶች መግዛትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን ይሰጣል ፤ ስለሆነም የካፒታል ዕቃዎች የሚገዙት በተፈቀደው ካፒታል በጀት መሠረት ይሆናል ፤

ለ) ቼኮችንና ሌሎችም የንግድ ሰነዶችን ያረጋግጣል፤ ይፈርማል ፤

ሐ) የመንግሥት መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከውጪ አገር ሆነ ከአገር ውስጥ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት ካለው ከማናቸውም ድርጅት ጋር ይዋዋላል ፤

መ/ ድርጅቱን በተቀላጠፈ አኳኋን ለማካሄድ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣኑን ብቁ ለሆነ ለማናቸውም የድርጅቱ ሠራተኛ በውክልና ይሰጣል ፤

፭/ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አዋጁንና በአዋጁም መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በጥብቅ በመከተል ተግባሩን በትጋትና ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ይፈጽማል ፤

፮/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያገናኙት ጉዳዮች ሁሉ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ማናቸውንም ድርጅቱን ለማስተዳደር ፤ ለመምራት እና የድርጅቱን ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልጉትን ሥራዎች ሁሉ ለመሥራት ሙሉ ሥልጣን እንዳለው ይቆጠራል ።

## ፱፤ የሒሳብ መዝገቦችና ሰነዶች አያያዝ ፤

፩/ እያንዳንዱ ድርጅት በንግድ ሥራ ልምድና ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት አስፈላጊ የሆኑ የሂሣብ መዝገቦችና ሰነዶች መያዝ አለበት።

፪/ ከቍጥር ፷፮ እስከ ፸ እንዲሁም ከቁጥር ፸፬ እስከ ቍጥር ፹፭ ያሉት የ፲፱፻፶፪ ዓ. ም. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ቍጥሮች ለየድርጅቱ የሂሣብ መዝገቦችና ሰነዶች አያያዝ አስፈላጊው ለውጥ ተደርጎላቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ ፤

(a) borrow money;

(b) sell, pledge and mortgage fixed assets such as buildings, furniture, fixture, and vehicles;

(c) withdraw deposits from bank accounts;

(d) settle disputes out of court.

(3) The General Manager shall:

(a) open bank account and make deposits;

(b) represent or appoint a person to represent in any legal proceedings brought by or against it;

(c) draw up and submit for the Authority's approval the internal regulations of the corporation; and

(d) employ and discharge any employee of the corporation and fix their salaries and remuneration with the Authority's approval.

(4) The General Manager shall, in accordance with general directives to be issued by the Authority:

(a) make decisions relating to operation, production of crops, production of goods and provision of services, sale of crops and goods and procurement of the necessary goods and services, provided that procurement of capital goods shall be within the limit of the approved capital budget;

(b) sign and countersign cheques and other commercial instruments;

(c) without prejudice to government directives, enter into contracts with any natural or juridical person, foreign or domestic;

(d) delegate any of this authority to any qualified person employed by the corporation whenever he deems it appropriate for the efficient management of business;

(5) The General Manager of each corporation shall perform his duties with due care and diligence and in strict compliance with the Proclamation and regulations issued thereunder.

(6) In his relations with third parties, the General Manager shall be deemed to have full power to carry out all acts of management of the corporation.

## 9. *Keeping of Books and Accounts*

(1) Each corporation shall keep such books and accounts as are required in accordance with business practice and guidelines to be established by the Authority.

(2) The Provisions of Article 66 to 70 and Articles 74 to 85 of the Commercial Code of Ethiopia of 1960 shall apply *mutatis mutandis* to the keeping of books and accounts of each corporation.

**፲፡ የበጀት ዓመት ፡ ሂሳቦችና ዓመታዊ መግለጫዎች ፡**

፩/ የእያንዳንዱ ድርጅት የበጀት ዓመት በየዓመቱ በመጋቢት ሠላሳ (፴) አልቆ በሚያዝያ አንድ (፩) ይጀመራል ።

፪/ በእያንዳንዱ የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የየድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ባለሥልጣኑ በሚፈቅደው ዘዴ በመጠቀም በድርጅቱ ያሉትን ልዩ ልዩ ንብረቶችና ያሉበትን ዕዳዎች የሚያመለክት የንብረት ዝርዝር መዝገብ ያዘጋጃል ።

፫/ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፡ ገንዘብ ነክ መግለጫዎች ፡ የሂሣብ ሚዛን ፡ የትርፍና የኪሣራ ሂሣብ እንዲሁም ባለፈው የበጀት ዓመት ስለነበረው የድርጅቱ ሁኔታና አሠራር አንድ ራፖር ያዘጋጃል ። ራፖሩም ስለትርፍና ኪሣራው ሂሣብ ዝርዝር ማብራሪያ የገንዘቡን ምንጭ እና የአጠቃቀሙን ሁኔታ እና የየድርጅቱን የኢኮኖሚ አቅዋም ለማወቅ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች መያዝ አለበት ።

፬/ የንብረቱ ዝርዝር ፡ ገንዘብ ነክ መግለጫው ፡ የሂሣቡ ሚዛን ፡ የትርፉንና የኪሣራውን ሂሣብ ፡ እንዲሁም ከዚህ በላይ ባለው ንዑስ አንቀጽ መሠረት የተዘጋጀው ራፖር ያለፈው የበጀት ዓመት በተፈጸመ በስድስት (፮) ወር ውስጥ ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት ።

፭/ የሂሣብ ሚዛኑ እና የትርፍና የኪሣራ ሂሣቡ በባለሥልጣኑ ከጸደቀ በኋላ ታትሞ ይወጣል ።

10. *Fiscal Year, Accounts and Annual Reports*

(1) The fiscal year of each corporation shall end on the thirtieth (30th) of Megabit and begin on the first (1st) of Miazia, each year.

(2) At the end of each fiscal year the General Manager of each corporation shall prepare a detailed inventory and valuation of assets and liabilities by using such methods as the Authority may approve.

(3) The General Manager of each corporation shall draw up financial statements, balance sheet and profit and loss accounts and prepare a report on the state of the activities and affairs of the corporation during the last fiscal year which report shall include detailed information on the profit and loss accounts, source of revenue and conditions of expenditure and such other information as is necessary to determine the economic viability of the corporation.

(4) The inventory, financial statements, balance sheet, profit and loss account and the report prepared in accordance with the preceding sub-article shall be submitted to the Authority within six (6) months after the close of the last fiscal year.

(5) The balance sheet and profit and loss account shall be published after approval of the same by the Authority.

**፲፩፡ የበጀት መጠየቂያ ፡**

እያንዳንዱ ድርጅት የበጀት ዓመት ከማለቁ ከስድስት (፮) ወር በፊት የልማት በጀቱንም የሚጨምር የበጀት መጠየቂያ ካስፈላጊው ፕላን ጋር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት ።

11. *Budget Proposals*

Each corporation shall, six (6) months before the end of each fiscal year, submit to the Authority its budget proposal, including development budget with the necessary plan.

**፲፪፡ የሥራ ዝርዝር መግለጫ ፡**

ይህ ደንብ ከጸናበት ጊዜ አንስቶ እያንዳንዱ ድርጅት በየሶስት ወር የሥራውን ዝርዝር ሁናቴ የሚገልጽ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው መደበኛ ፎርም መሠረት ለባለሥልጣኑ ራፖር መስጠት አለበት ።

12. *Report of Activities*

Each corporation shall submit to the Authority a report of its activities every three (3) months starting from the effective date of these Regulations in a standard form to be prepared by the Authority.

**፲፫፡ መጠባበቂያ ሂሣቦች ፡**

፩/ እያንዳንዱ ድርጅት የመጠባበቂያ ሂሣብ በማቋቋም የመጠባበቂያ ሂሣቡ ከድርጅቱ ዋና ገንዘብ ከመቶ ሰላሣ /፴/ እጅ እስከደረሰ ድረስ በየዓመቱ ከተጣራው ትርፍ በመቶ አስር (፲) እጅ ያስቀምጣል።

፪/ በማናቸውም ዓመት ኪሣራ ቢደርስ ከመጠባበቂያው ሂሣብ ገንዘብ ወጭ በማድረግ ኪሣራው ይተካል፤ ስለሆነም የመጠባበቂያው ሂሣብ መጠን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው በታች የሆነ እንደሆነ ጉድለቱ በተከታታይ ዓመታት ይተካል ።

13. *Reserve Funds*

(1) Each corporation shall set aside ten per cent (10%) of its net profits in order to establish and maintain a reserve fund until such time as the reserve fund shall attain a sum equal to thirty per cent (30%) of each corporation's capital.

(2) Should the profit and loss account of any corporation show a loss for any particular year, such loss shall be covered by drawing from the reserve fund, provided that transfers shall be made in accordance with the preceding sub-article to the reserve fund in subsequent years, where it has fallen below the amount fixed in the preceding sub-article.

**፲፬፡ ስለሂሣብ መርማሪዎች ፡**

፩/ የየድርጅቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ የሆነ ነገር ሁሉ በዋናው ኦዲተር ወይም በሱ በሚመረጡ የሂሣብ መርማሪዎች በየዓመቱ ይመረመራል ።

፪/ ዋናው ኦዲተር በማንኛውም ጊዜ የየድርጅቱን የሂሣብ መዛግብት ለመመርመር ይችላል ።

14. *Auditors*

(1) The books of account and all financial matters of each corporation shall be audited annually by the Auditor-General or by auditors designated by the Auditor-General.

፫/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በየዓመቱ የሚደረገው የሂሣብ ምርመራ መግለጫ የበጀቱ ዓመት እንደተፈጸመ በስድስት (፮) ወር ውስጥ ለባለሥልጣኑ እና ለዋናው ኦዲተር ይቀርባል ።

**፲፭። ስለድርጅት መፍረስ ።**

፩/ አንድ ድርጅት የሚፈርስበት በቂ ምክንያት ካለ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀ በኋላ ፈራሽ ይሆናል ።

፪/ አንድ ድርጅትን ለማፍረስ በቂ ምክንያት የሚኖረው የድርጅቱ የኢኮኖሚ አቅዋም ለመኖር የማያስችለው የሆነ እንደሆነ ወይም የድርጅቱን ሕልውና የሚነካ ውሳኔ ከመንግሥት የተሰጠ እንደሆነ ነው ።

**፲፮። ስለ ድርጅት ሂሣብ መጣራት ።**

፩/ አንድ ድርጅት እንዲፈርስ ከተወሰነ ባለሥልጣኑ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የውጭ ሂሣብ አጣሪዎች ይሾማል ።

፪/ ሂሣብ አጣሪው ወይም፤ እንደነገሩ ሁኔታ፤ ሂሣብ አጣሪዎቹ በመፍረስ ላይ ያለውን ድርጅት የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች ለማየትና ለመመርመር ሥልጣን ይኖራቸዋል ። ስለሆነም የድርጅቱን ንብረት ለመቆጣጠርም ሆነ ሥራውን ለመምራት ሥልጣን አይኖራቸውም ።

፫/ በመፍረስ ላይ ያለው ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ካለፈው የበጀት ዓመት መጨረሻ እስከ ሂሣብ ማጣሪያው ጊዜ ድረስ ስላለው ስለድርጅቱ የሥራ አካሄድ ለሂሣብ አጣሪው ወይም፤ እንደነገሩ ሁኔታ፤ ለሂሣብ አጣሪዎቹ መግለጫ ያዘጋጃል ።

፬/ ሂሣብ አጣሪው ወይም፤ እንደነገሩ ሁኔታ፤ ሂሣብ አጣሪዎቹ እና ዋናው ሥራ አስኪያጅ የንብረቶቹን እና የዕዳዎቹን ዝርዝር በአንድነት ያዘጋጁና ይፈርሙበታል ።

፭/ ሂሣብ አጣሪው ወይም፤ እንደነገሩ ሁኔታ፤ ሂሣብ አጣሪዎቹ የሂሣብ ሚዛን አዘጋጅተው ለባለሥልጣኑ ያቀርባሉ ።

፮/ ባለሥልጣኑ ድርጅቱ እንዲፈርስ የተወሰነ መሆኑን ታትመው በሚወጡ በሀገሪቷ ጋዜጦች በአማርኛና በእንግሊዝኛ በወር አንድ ጊዜ በተከታታይ ለሶስት ወር በማሳተም ባለገንዘቦቹ የይከፈለን ጥያቄአቸውን እንዲያቀርቡ በሚገባ ያስታውቃቸዋል ። በድርጅቱ መዝገቦች ውስጥ ለተጻፉት ወይም በሌላ አኳኋን አድራሻቸው ለታወቀ ባለገንዘቦች ግን የድርጅቱ መፍረስ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከመታተሙ በፊት በሬኮማንዴ ደብዳቤዎች ይልክላቸዋል ።

፯/ ባለሥልጣኑ የሂሣብ አጣሪውን ወይም፤ እንደነገሩ ሁኔታ፤ የሂሣብ አጣሪዎቹን አስተያየት በሚገባ ካመዛዘነ በኋላ ጥያቄአቸውን የሚደግፍ ማስረጃ ለሚያቀርቡት ባለገንዘቦች በሂሣብ ሚዛን መሠረት ገንዘባቸውን ይከፍላቸዋል ።

(2) The Auditor-General may, at any time, audit the books of account and all financial matters of any corporation.

(3) The report of the auditors in accordance with sub-article (1) of this Article shall be submitted to the Authority and the Auditor-General within six (6) months from the close of the fiscal year.

15. *Grounds For Dissolution*

(1) A corporation may, with the approval of the Council of Ministers, be dissolved for good cause.

(2) There shall be good cause for dissolution where the corporation is not economically viable or where any decision affecting the existence of the corporation is passed by the government.

16. *Winding Up*

(1) The Authority shall appoint one or more external liquidators where a decision to dissolve a corporation is passed.

(2) The liquidator or liquidators, as the case may be, shall have power to examine the books of accounts of the corporation under dissolution. They shall not, however, have power to take possession of the property, nor act as managers of such corporation.

(3) The General Manager of the corporation concerned shall prepare a report for the liquidator or the liquidators, as the case may be, on the management of the corporation from the end of the last fiscal year to the date of the winding up.

(4) The liquidator or the liquidators, as the case may be, and the General Manager shall jointly prepare and sign an inventory of assets and liabilities.

(5) The liquidator or liquidators, as the case may be, shall prepare a balance sheet and submit the same to the Authority.

(6) The Authority shall duly notify all creditors of the proposed dissolution of the corporation and require them to file their claims in a notice published in the country's newspapers in Amharic and English once every month, consecutively for three months. However, creditors appearing in the corporation's books or who are otherwise known shall be notified of the dissolution by registered letter prior to the publication of the notice of dissolution in the newspapers.

(7) The Authority shall, on the basis of the balance sheet, pay the creditors who produce proof of their claims after due consideration of the recommendation of the liquidator or liquidators, as the case may be.

፰/ ድርጅቱ ያልፈጸማቸው ጅምር ሥራዎች ካሉ እስኪፈጸሙ ድረስ የድርጅቱ መፍረስ ያልቆየ ከሆነ ወይም ገንዘብ ጠያቂዎች ያቀረቡት መረጃ በባለሥልጣኑ አስተያየት የጠየቁትን ገንዘብ ለመክፈል በቂ ሆኖ ሳያገኘው ቢቀር ገንዘብ ጠያቂዎቹ ላቀረቡት የገንዘብ ጥያቄ ባለሥልጣኑ በቂ ዋስትና ካልሰጣቸው ባለሥልጣኑ ድርጅቱ ያልፈጸማቸው ጅምር ሥራዎች ሲፈጸሙ ድርጅቱ የሚኖርበትን ዕዳ እና ያልተከፈላቸው ገንዘብ ጥያቄዎች የጠየቁትን ሂሣብ የሚሸፍን ገንዘብ በተለይ ማስቀመጥ አለበት ።

፱/ የድርጅቱ ባለገንዘቦች ከተከፈሉ በኋላ ሂሣብ አጣሪው ወይም እንደነገሩ ሁኔታ፤ ሂሣብ አጣሪዎቹ ከዕዳ የተረፈ ንብረት ካለ ይህንኑ የሚያሳይ የመጨረሻ የሂሣብ ሚዛን አዘጋጅተው ለመንግሥቱ ዋና ኦዲተር ግልባጭ በማድረግ ለባለሥልጣኑ ያቀርባሉ ። ባለሥልጣኑ የመጨረሻውን የሂሣብ ሚዛን ካጸደቀው በኋላ ወዲያውኑ ስለድርጅቱ መፍረስ በነጋሪት ጋዜጣ ማስታወቂያ ያወጣል ። ማስታወቂያ ሲወጣ የድርጅቱ ሕልውና ይቀራል ።

፲/ የፈረሰው ድርጅት መዝገቦች የመጀመሪያው ገንዘብ ጠያቂዎች ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በባለሥልጣኑ ይቀመጣሉ ።

፲፩/ ባለሥልጣኑ የሚወስነውን ገንዘብ በመክፈል ማንም ሰው እነዚህን መዝገቦች ሊመረምር ይችላል።

፲፯ ፣ መቀላቀል ፣

፩/ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ድርጅቶች አንዱ ሌላውን ወይም ሌሎቹን በመጠቅለል ወይም ሌላ ድርጅት በማቋቋም በባለሥልጣኑ ውሳኔ ሊቀላቀሉ ይችላሉ።

፪/ ባለሥልጣኑ ድርጅቶችን ለመቀላቀል የሚሰጠው ውሳኔ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ይወጣል ።

፫/ ጠቅላዩ ድርጅት ወይም በመቀላቀል የተገኘው አዲስ ድርጅት የቀሩት ድርጅቶች መብትና ግዴታ በሙሉ ይወርሳል ።

፲፰ ፣ ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ ፣

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፩ ቀን ፲፱፻፸ ዓ. ም.

ዘገየ አስፋው

የእርሻና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስትር

(8) Where there are undertakings not completed by the corporation and the dissolution cannot stay until the completion of such undertakings or where, in the opinion of the Authority, the evidence produced by creditors is not sufficient to support their claims and the Authority cannot give adequate guarantee for the claims of such creditors, the Authority shall set aside a sum that covers the liabilities of the undertaking not completed and the claims of creditors not settled.

(9) After the creditors of the corporation have been paid the liquidator or liquidators, as the case may be, shall prepare a final balance sheet showing the surplus assets, if any, and submit the same to the Authority, with a copy to the Auditor-General of the Government. As soon as the Authority approves the final balance sheet, it shall publish notice of dissolution of the corporation in the Negarit Gazeta. The corporation shall cease to exist upon publication of the notice.

(10) The books of a corporation which has been dissolved shall be deposited with the Authority where they shall be kept for five years starting from the publication of the first notice in the country's newspapers calling creditors.

(11) Such books shall be open to inspection by any person after payment of a fee prescribed by the Authority.

17. *Amalgamation*

(1) Two or more corporations may be amalgamated by decision of the Authority either by taking over or by the formation of a new corporation.

(2) The decision to amalgamate shall be published in the Negarit Gazeta.

(3) The claims and liabilities of the corporation ceasing to exist shall pass to the corporation taking over or to the new corporation resulting from the amalgamation.

18. *Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the 1st day of Miazia, 1970 (E.C.)

Done at Addis Ababa, this 9th day of May, 1978

*ZEGEYE ASFAW*

*Minister of Agriculture and Settlement*